# ሕዝባዊ ተጋድሎ


THE
NATIONAL

# ህዝባዊ ተጋድሎ ምንድን ነው?

**ተርጓሚ: ዮሐንስ ሞላ**

ሕዝባዊ ተጋድሎ (civil resistance)፥ ሰፊው ሕዝብ ካለምንም ሃይል እርምጃ፣ ስለመብቶቹ፣ ስለነጻነቱ እና ስለፍትህ መከበር የሚታገልበት መንገድ ነው። በሕዝባዊ ተጋድሎዎች ላይ የሚሳተፉ ሰዎች፥ መጠነ ሰፊ የሆነ የማኅበረሰብ፣ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ለውጥ እንዲኖር፥ እንደ አመጽ፣ ምርት እና አገልግሎትን ተጠቃሚ እንዳያገኝ ማጣጣል (ቦይኮት ማድረግ)፣ ብዙዎች የሚሳተፉበት ሰልፍ እና ተቃውሞ፣ እንዲሁም ሌሎች ዓይነት ተግባራትን ይጠቀማሉ። የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። በዓለም ዙሪያ፥ ሕዝባዊ ተቃውሞ በተለያዩ ስሞች ይጠራል። ሰላማዊ ትግል (nonviolent struggle)፣ ቀጥተኛ እርምጃ (direct action)፣ ሕዝባዊ ኃይል (people power)፣ ፖለቲካዊ እምቢተኝነት፣ እና ሕዝባዊ የክተት ጥሪ፥ ተብሎ ይጠራል። ሆኖም ግን፥ በየትኛውም ዓይነት ስያሜ ቢጠራ፥ የሕዝባዊ ተቃውሞ መሰረታዊ እንቅስቃሴ ተመሳሳይ ነው።

የቀድሞውን ስርዓት ለመተግበር በታማኝነት የመንቀሳቀስ አዝማሚያ ላላቸው ሕዝቦች፥ በአንጻሩ ነጻ የሆነ እና አግባብ ያለው አዲስ የማኅበረሰብ ራዕይን በማቅረብ፣ ጭቆናን ለመቋቋም ለብዙሀን ተሳትፎ ጥሪ ስለሚያደርጉ፥ የሕዝባዊ ተጋድሎ ንቅናቄዎች ከፍተኛ አቅም አላቸው። ሕዝቦች ኢፍትሀዊ ከሆኑ መሪዎች ጋር ያላቸውን ትብብር ለማቋረጥ ሲወስኑ፥ ስርዓቱ ለመቀጠል ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍለው ይሆናል። ሕዝቦች እምቢተኝነትን ሲያሳዩ፥ ስርዓቱ ዘላቂነትን ስለሚያጣ፣ ወይ ስርዓቱ ይለወጣል ወይ ደግሞ ይወድቃል። የሕዝባዊ ተቃውሞ ተቀናቃኞች በደንብ የታጠቁ ወይንም ብዙ የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙ በሚሆኑበት ጊዜ እንኳን፥ በአብዛኛው ጊዜ፣ ስልታዊ በሆነ መልኩ የተስፋፉ የሰላማዊ ትግል እምቢተኝነቶች የፈጠሯቸውን፥ ዘላቂነት ያላቸውን ብዝሀ እምቢተኝነትን እና ሕዝባዊ ነውጥን በጽናት መቋቋም አይችሉም።

በዚህም ምክንያት ብዙ የሕዝባዊ ትግል እንቅስቃሴዎች እና ዘመቻዎችየተለያዩ ባላንጣዎቻቸውን ተቋቁመው ስኬታማ ሆነዋል። ባለፈው ክፍለዘመን፥ በሁሉም አስርት ዓመታት ውስጥ፣ በስድስት አህጉራት ውስጥ፣ የሰላማዊ ትግል ብልሀቶችን የተጠቀሙ ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ጨቋኝ ስርዓቶችን ጥለዋል፣ የወታደራዊ ኃይሎችን በስኬት ተቋቁመዋል፣ እንዲሁም ለማኅበረሰቦቻቸው ከፍተኛ የሆነ ፍትህ እና ነጻነት አምጥተዋል። ለምሳሌ፥ ሕዝባዊ ተቃውሞ የደቡብ አፍሪካን የአፓርታይድ ስርዓት ለማስቆም ቁልፍ ነበር፤ አሜሪካ ውስጥ የሴቶችን መብቶች፣ የሕዝብን መብት እና የላብ አደሮችን መብቶች ወደፊት በማራመድ ጥቅም ላይ ውሎ ነበር፤ ፊሊፒንስ፣ ቺሊ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ሰርቢያ እና ሌሎች ቦታዎች ያሉ አምባገነኖችን ጥሏል፤ ምስራቅ ቲሞር እና ዴንማርክ ውስጥ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ለማሰናከል ጠቅሟል፤ የሕንድን ነጻነት ከእንግሊዝ ለማግኘት ዓይነተኛ መንገድ ሆኖ አገልግሏል፤ ምስራቅ አውሮፓ ውስጥ የነበሩ የተጭበረበሩ ምርጫዎችን ሂደት ቀይሯል፣ ሊባኖስ ውስጥ የሶሪያን ጣልቃ ገብነት አስቁሟል፣ እንዲሁም በሌሎች በርካታ ቦታዎች የሰብዓዊ መብቶችን፣ ፍትህን እና ዴሞክራሲያዊ የራስ ገዝ አስተዳደርን ለማስፈን ጥቅም ላይ ውሏል።

### መሰረታዊ ሀሳቦች

### ሕዝባዊ ተቃውሞ እና ግብረገባው ኃይል አልባ ትግል

ሕዝባዊ ተቃውሞ የፖለቲካዊ ውዝግብ ዓይነት ነው። ግብረገባዊ ሰላማዊ ትግል፥ ሁከት እና ብጥብጥን መጠቀም የሚከለክሉ መርሆች ስብስብ ነው። እንደ የህንድ የነጻነት ትግል እና የአሜሪካ ሕዝባዊ መብቶች እንቅስቃሴዎች የመሳሰሉ፣ ስኬታማ የሆኑ የሕዝባዊ ትግል እንቅስቃሴዎች ተሳታፊዎች፣ ግብረገባዊ

ሰላማዊ ትግልን ሰብከው ነበር። ነገር ግን፥ የሕዝባዊ ሰላማዊ ተጋድሎዎችን በመጠቀም ዙሪያ፥ ተሳታፊዎቹ ለስኬታማነቱ ሲሉ ከሁከት እና ብጥብጥ ነጻ የሆኑ መንገዶችን ሙጢኝ እንዲሉ የሚያደርግ ተፈጥሯዊ ውርስ የለም። በርግጥ፥ በታሪክ ውስጥ፥ አብዛኛዎቹ የሕዝባዊ ታጋዮች በግብረገባዊ የሰላማዊ ትግል የተነቃቁ አልነበሩም። ይልቅስ፥ ሕዝባዊ ተቃውሞ ትግላቸውን ውጤታማ ለማድረግ ብቸኛው እና ዋናው ውጤታማ መንገድ መሆኑን በማወቃቸው ነበር የተነቃቁት።

## አንድ ወጥ የሆነ እና ዘርፈ ብዙ የኃይል እይታዎች

በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ፥ ነባራዊው የስልጣን አመለካከት አንድ ወጥ የሆነ እና ከመንግስት ስርዓት በቀጥታ ወደ ሕዝብ የሚወርድ ነው። ይኸም ማለት፥ ተራው የህብረተሰብ ክፍል በመንግስታቸው እና በተቋማቶች በጎ ፈቃድ፣ ውሳኔ እና ድጋፍ ላይ ጥገኛ እንደሆኑ የሚታይበት ነው። ስልጣን ጥቃት ለመፈጸም ከፍተኛው የሆነ ሀብት እና አቅም ያላቸው፣ የአዛዥነት ማማ ላይ የቆሙ ጥቂት ሰዎች በሙሉ ኃይላቸው የሚያስተዳድሩበት መሳሪያ እንደሆነ ነው የሚቆጠረው። አንድ ወጥ የሆነና ከመንግስት ወደ ሕዝብ የሚወርድ የስልጣን/ኃይል ስርዓት፥ አድራጊ ፈላጭ ቆራጭነት፣ ዘላቂ እና በቀላሉ የማይለወጥ ተደርጎ ነው የሚታየው። ሆኖም ግን፥ ሕዝባዊ ተጋድሎ፥ ጣምራ በሆነ እና ከሕዝብ ወደ ስርዓት ሊሄድ በሚችል የስልጣን/ኃይል አተያይ የሚገለጽ እና መንግስታትን ወይም ሌሎች ስልጣን ያላቸው ስርዓቶች በሕዝብ ፈቃደኝነት እና መስማማት ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ የሚያሳዩ የተለዩ መርሆች ላይ የተመሰረተ ነው። ልዩ ልዩ ሕዝቦች እና መርሆችን በሚያሳትፈው አተያይ፥ ስልጣን/ኃይል አብዛኛውን የሕብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ እና መተማመኛ መሰረት ያደረገ ነው። እንዳስፈላጊነቱ የሚለዋወጥ እና፣ ሁልጊዜም የመነሻ ምንጮቹ የመለዋወጥ አቅም፣ በብዙ ሰዎች እና ተቋማት ተሳትፎ የተመሰረተ ነው። የሕዝባዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ብልሀቶቻቸውን አጠናክረው የሚያሳድጉት፣ የመንግስትን ተግባሮች ለማናወጥ፣ ሰፊ የሆነ መደበኛ ዜጎች ጥምረት በሚያስተባብሩ ሰዎች ዋጋ ቢስ ሊያደርጉትም፣ ሊለውጡትም ይችላሉ በሚለው እይታ በመመስረት ነው።

## ያለመታዘዝ ድርጊት እና የማይፈቀዱ ድርጊቶችን መፈጸም

በታሪክ ውስጥ፥ ሕዝባዊ ተቃዋሚዎች በመቶዎች የሚቆጠሩ ልዩ ልዩ ታክቲኮችን ተጠቅመዋል። እነዚህ ይትግል ስልቶች በሁለት የተለያዩ ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ። አንደኛው ያለመታዘዝ ሁኔታ (acts of omission) ሲሆን፥ ይኸም ሰዎች በመደበኛ ሁኔታ ያደርጉታል ተብሎ የሚታሰብ፣ ወይም እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸውን ማድረግ ሲያቆሙ ነው። ለምሳሌ፥ የሰራተኞች አድማ፣ የግብር መክፈል እምቢተኝነት እና እቀባ (boycotts) ይጠቀሳሉ። ሌላኛው ደግሞ የማይፈቀዱ ድርጊቶችን መከወን (acts of commission) ሲሆን ይኸም ሰዎች በመደበኛ ሁኔታ ወይም ወቅት የማያደርጓቸውን ወይም እንዲያደርጉ የማይፈቀድላቸውን ነገሮች ማድረግ ሲጀምሩ ነው። ለምሳሌ፥ ተቃውሞዎች፣ ብዙሀንን የሚያሳትፍ ሰላማዊ ሰልፍ እና የአደባባይ ተቃውሞ፣ ቤት ውስጥ የመዋል አድማ እና ሌሎች ዓይነቶች የሕዝባዊ እምቢተኝነት ተግባራት ይጠቀሳሉ። የእነዚህ ዓይነት የሰላማዊ ተቃውሞ ዘዴዎች ዕቅዳዊ ቅደም ተከተል፥ የእንቅስቃሴዎቹ ተቃዋሚ አካል፣ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ጠብቆ ለማቆየት የሚያወጣውን ዋጋ በጣም ከፍ ያደርግበታል። የተቃውሞ ዘዴዎቹ ዓይነት፥ ከፍተኛ ከሆነ እስከ ዝቅተኛ ስጋት ድረስ፣ ከሕዝባዊ እስከ ግለሰብ፣ በጋራ ከሚመጣ እና በተበታተነ መልኩ እስከሚሆን፥ ድረስ ልዩ ልዩ መልክ ያለው ስለሚሆን፣

ሰፊው ሕዝብ ተቃውሞዎቹን እንዲቀላቀል ሊያነሳሳ ይችላል፤ ከሕብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎችም ሰዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል።

**አንድነት፣ ዕቅድ እና የሰላማዊ ግብረገብነት**

የስኬታማ ሕዝባዊ ተቃውሞ ሶስት ቁልፍ መርሆች፥ አንድነት፣ እቅድ እና የሰላማዊ ግብረገብነት ናቸው። አንድነት፥ በመጀመሪያ በአንድ የተለየ ዓላማ ዙሪያ፥ የተለያየ ዓይነት ቁጣ እና አመለካከት ሊኖራቸው ይችሉ የነበሩ የማኅበረሰብን ልዩ ልዩ ክፍሎችን ለክተት በማንቀሳቀስ የሚዳብር ነው። ዕቅድ፥ የእንቅስቃሴዎችን ሁኔታዎች እና ዕድሎችን በጥንቃቄ በማጤን እና በመተንተን ላይ የተመሰረተ፣ የዘመቻዎች እና ዘዴዎች ስልታዊ ቅደም ተከተል ነው። ከዚህ በተጨማሪ፥ ሊከወኑ የሚችሉ ማፈግፈጎችን እና ለእነሱ የሚሆኑ አማራጭ እቅዶችን ሊያካትት ይችላል። የሰላማዊነት ስነስርዓት የሰላማዊ ዘዴዎችን ብቻ ለመጠቀም ስልታዊ ቁርጠኝነትን ያካተተ ነው። ምክንያቱም፥ ሁከት እና ብጥብጥ፣ የሕዝብን ተሳታፊነት ይቀንሳል፣ የሰላማዊ ትግሉን እንቅስቃሴ ታማኝነት ሊጎዳው ይችላል፣ ዓለማቀፍ ድጋፍን ሊቀንስ ይችላል፣ እንዲሁም የለውጡን ታማኝነት የመቀነስ ዕድል ሊኖረው ይችላል።

<u>**አስር ጥያቄዎች**</u>

**1. ሃይለኛ መሪዎች ሕዝባዊ ተቃውሞን የሚሸነፉት እንዴት ነው?**

*ማንኛውም መሪ ተፈጥሯዊ ኃይለኝነት የለውም። መሪዎች ኃይለኛ እና አቅም ያላቸው የሚሆኑት፥ በማኅበረሰብ ውስጥ፣ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ በሺህዎች ወይም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሕዝቦች ድጋፍ ሲኖራቸው ነው። መሪዎቹ ቁጥጥርን፣ የፖሊስ ሰራዊትን፣ ወታደራዊ ስርዓትን፣ የፍትህ ስርዓትን እና የቢሮክራሲ አስተዳደር ባለበት ጠብቆ ለማቆየት፥ ሕዝቦች ሥራቸውን መስራት አለባቸው። ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ሕዝቦች በመደበኛነት ወደ ስራ መሄድ አለባቸው፣ ግብር እና ኪራይ መክፈል አለባቸው፣ እንዲሁም ገበያ ላይ በመንግስት የተያዙ እና የመንግስት ፈቃድ ያላቸውን ንግዶች ድጋፍ የሚያደርጉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶችን መገባየት ይኖርባቸዋል። በእቃ እና ሰው ማጓጓዝ ላይ የሚሰሩ ሰዎች፣ እንዲሁም በግንኙነት ዘርፍ እና በአገልግሎት ሰጪነት የሚያገለግሉ ሰዎች እቃዎችን ማንቀሳቀስ እና አገልግሎቶችን ማከናወን ይኖርባቸዋል። እነዚህ፥ ስርዓቱ እንዲቆይ ወሳኝ ሆኖ እንዲቆይ፣ በአብዛኛው ድጋፋቸው ወሳኝ የሆኑ ቡድኖች መካከል ለምሳሌ ያነሳናቸው ጥቂቶቹ ናቸው።*

*ይኸንንም በመረዳት፥ የሕዝባዊ ተቃውሞዎች አስተባባሪዎች ያንን ድጋፍ የሚያናውጥ እና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ዘላቂ እንዳይሆን የሚያደርጉ ዘዴዎችን ይፈጥራሉ። በተለይ ጭቆና ሰዎች መብቶቻቸውን እንዳይጠቀሙ ለማገድ በሚውልበት ጊዜ፣ ለተቃውሞ በርካታ ቁጥር ያላቸውን ሰዎችን ማስተባበር እና ለክተት መጥራት የመሪዎችን ተአማኒነት ይቀንሳል። የመንግስትን ተቆጣጣሪነት በማነዋወጥ፣ የስርዓቱ ተከላካዮች እና ተሟጋቾች ሳይቀሩ የወደፊት ዕጣ ፈንታውን በሚመለከት ጥያቄ ማንሳት እስኪጀምሩ ድረስ፥ የተጋድሎ እንቅስቃሴዎች፥ ስርዓቱን ጠብቆ ለማቆየት የሚያስከፍለውን ዋጋ ያፋጥናሉ። አንድ ጊዜ ታታአማኒነታቸው መቃለል ከጀመረ ደግሞ፥ ማንኛውም ዓይነት የጭቆና መንገድ ቢሆን ስኬታማ ለመሆን አስቸጋሪ ይኾናል።*

## 2. ሕዝባዊ ተቃውሞ እንዴት ይጀምራል?

በርካታ ስኬታማ የሆኑ ሕዝባዊ የተቃውሞ ዘመቻዎች የጀመሩት፥ በመጀመሪያ የተራውን ሕዝብ እርምጃ የመውሰድ አቅም በቅድሚያ በመገንባት ነው። አገር በቀል የሆኑ፣ ሕዝብን ለማደራጀት እና አንድነትን ለመገንባት፥ ስጋት እና ጉዳታቸው ዝቅተኛ የሆኑ ዘዴዎችን መጠቀም አስደናቂ በሆነ መልኩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፥ ጋንዲ ሕንድ ውስጥ የመጀመሪያውን የሕዝባዊ ተቃውሞ ዘመቻ ከመጀመሩ በፊት፥ ተራውን ሕዝብ በማናገር እና በመጎብኘት፣ የሕዝቡን ስሜት፣ ኀዘን፣ ተስፋ እና ፍርሀቶች በማጤን እና ይበልጥ በመረዳት ወራት እና ዓመታትን አሳልፏል። የሕዝቡን ታማኝነት እና ተባባሪነት ማግኘት የሚያስችለውን ስሜትም ገንብቷል። በመንግስት አስተዳደር ውስጥ በራስ መተማመናቸውን ያጡ እና ቀድሞ እርምጃ ለመውሰድ አቅመቢስነት ይሰማቸው የነበሩ ሕዝቦች ዘንድ፣ በራስ መተማመንን መገንባት የሚያስችል ገንቢ የሆኑ የኅብረተሰብ አገልግሎቶች ውስጥ እንዲሳተፉ አበረታቷል።

አንዴ ዘመቻዎች ቀጥተኛ የሆነ ሕዝባዊ ተቃውሞ ላይ ለመሰማራት የሚያስችላቸውን በቂ አቅም ከገነቡ፣ ብዙ ጊዜ የአገር በቀል ጉዳዮችን ለብዙሀን በሰፊው ማስተጋባት ላይ ከሚያነጣጥሩ ተግባራት ይጀምራሉ። ለምሳሌ፥ ፖላንድ ውስጥ የአንድነት ይሰራተኛ ንቅናቄ (Solidarity) ያደራጁት ሰዎች፣ በአንድ መርከብ ሥራ የተሰማሩ ወዛደሮችን ሥራ እንዲያቆሙ በማሳደም ነበር እንቅስቃሴያቸውን የጀመሩት። የጋራ በሆነ ጉዳይ ላይ ድልን ሲቀዳጅ እና ገለልተኛ የሆነ የንግድ ማህበር ሲቋቋም፣ ይህ ድል በፖላንድ ነዋሪዎች ስነልቡና ላይ የፈጠረው ትልቅ ተጽዕኖ ነበር። ትግሉም ጥንካሬን ተጎናጽፏል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ የአሜሪካ የዜግነት መብቶች እንቅስቃሴ (Civil Rights Movement) እያየለ የሄደው፣ ስኬታማ የሆነ ወደየትም ያለመንቀሳቀስ፣ በመስማማት እና በአድማ በደቡብ አሜሪካ ጥቂት ከተሞች ላይ የሚታይ በሱቆች እና በአውቶብስ ውስጥ የነበረ የዘር ልዩነት እንዲያበቃ አድርጓል። በእነዚህ ስኬት፣ ትግሉ የሕዝባዊ ተቃውሞን ኃይል አሳይቷል። እንዲሁም በፍጥነት፣ ብሔራዊ ትኩረትን እና ክትትልን አስገኝቷል።

## 3. ተቃውሞ እንዴት ማደራጀት ይቻላል?

የአንድ የትግል እንቅስቃሴ ስልታዊ እቅድ አውጪዎች፥ ግባቸውን፣ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን፣ የባላንጣቸውን አቅም፣ እንዲሁም ሶስተኛ ወገኖች እና የውጭ አካላት ሊያበረክቱ የሚችሏቸውን ነገሮች መለየት ይገባቸዋል። አንድ ትግል፥ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ግቦቹን ግልጽ በሆነ መልኩ ሲወስን እና ሁኔታውን በዝርዝር እና በትክክል ሲያስቀምጥ፥ የትኛውን ዘዴ አገልግሎት ላይ ማዋል እንዳለበት ለመምረጥ ያመቸዋል፡፡ በዚህ ወቅት፣ ትግሉ እንደ ዋና ዘዴ በተቃውሞ ለሰላማዊ ሰልፍ ከተነሳ፣ እና እንዴት ስኬታማ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ትምህርት ለመቅሰም ካሰበ፥ በብልሃት እና በዘዴ ለመከወን ሊረዱ የሚችሉ ብዙ ምንጮች አሉ።

## 4. ተቃውሞዎች ካልሆኑ፥ ታዲያ ምን?

ብዙ ሰዎች፥ የሕዝባዊ ተቃውሞዎች፥ የሕዝባዊ ትግል እንቅስቃሴ ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን በትግል ሂደት ውስጥ ተቃውሞ ቀዳሚው ሳይሆን፣ ሕዝባዊ ታጋዮች በትግላቸው ወቅት ሊጠቀሟቸው ከሚችሏቸው በርካታ ዘዴዎች አንዱ ነው። ከሁለት መቶ በላይ፣ ኃይል አልባ የሆኑ፣

ተለይተው የታወቁ አማራጭ ዘዴዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል፥ በተለያየ መንገድ በሽማቾች ማእቀብ ማድረግ፣ ፖለቲካ እና ማኅበረሰብ ጉዳዮች ላይ አድማ ማድረግ፣ ሥራ ማቆም፣ ኪራይ ቀረጥ እና የአገልግሎት ገንዘብ አለመክፈል፣ አቤቱታ ማቅረብ፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነት፣ ያለመንቀሳቀስ አድማ፣ መተላለፊያ መንገዶችን መዝጋት፣ እንዲሁም የመሰል ሕዝባዊ ስብስብ ድርጅቶችን መቋቋም ይጠቀሳሉ።

የአንድን ትግል ዘዴ የመምረጥ እና ቅደም ተከተል የማስያዝ ስራ፥ የትግሉን ሁኔታዎች ግምገማ፣ እንዲሁም የትግሉን አቅም እና ዓላማ መሰረት ያደረገ ነው። ትግሉ በጣም ጠንካራ ካልሆነ፣ ምናልባትም የተበታተነ እና ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ሊቀንስ የሚችለውን ዘዴ መምረጥ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፥ አገልግሎትን ወይም ምርትን ላለመጠቀም አድማ እንደማድረግ፣ ወይም ማንነቱ ባልታወቀ ሰው የተቃውሞ ምልክቶችን ማሳየት ሊሆን ይችላል። ይኸ ደግሞ የእንቅስቃሴውን አቅም መገንባት፣ መልእክቶችን እርስበርስ መለዋወጥ እና ባላጋራን ለማወክ ይረዳል። እንዲህ እያለ ቀጥሎ በስተመጨረሻ፥ እንቅስቃሴው እየጠነከረ ሲሄድ፣ እንደ ሰላማዊ ሰልፍ፣ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች እና ሕዝባዊ እምቢተኝነት ያሉ፣ ይበልጥ የተጠናከሩ እና የተደራጁ እንቅስቃሴዎችን ሊተገብር ይችላል።

ሕዝባዊ ተቃውሞዎችን ለማከናወን ለሚያስቡ ሰዎች፣ እምቢተኝነት የተለመደ ድርጊት ስለሆነ ብቻ፣ ከሁሉም የተለየ እና ዋነኛ አካሄድ እንደሆነ ማሰብ ያልተገባ መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። እንደየሁኔታው የሚወሰኑ፣ የተለያዩ ገንዘብ ቆጣቢ እና የተሻለ ውጤት ያላቸው ዘዴዎች አሉ። የፈጠራ ክህሎት እና ብልሃት የታከለበት አስተሳሰብ፣ የትኛውን ዘዴ መጠቀም እንደምገባ ለመወሰን በጣም አስፈላጊ ናቸው።

### 5. ትግሉ ሞገስ ያለው መሪ ከሌለውስ?

በታሪክ ከተመዘገቡ ትግሎች መካከል፥ ይኸ ነው የሚባል ሞገስ ያለው መሪ ሳይኖራቸው ውጤታማ የሆኑ የሕዝባዊ ትግሎች ነበሩ። በደቡብ አፍሪካ ፀረ-አፓርታይድ ትግል፥ ምንም እንኳን መሪው ከትግሉ ተገልሎ እስር ቤት የነበረ ቢሆንም፣ ትልቅ ውጤት ያመጣ ነበር። ሞገስ ካለው ወይም የንግግር ችሎታው ከላቀ መሪ ይልቅ፣ በትግል ውስጥ የእንቅስቃሴውን ተሳታፊዎች እንዴት እንደሚወክል እና እንደሚያዳምጥ የሚያውቅ፣ የሚከፈሉ ዋጋዎችን እና የሚኖሩ አደጋዎችን የሚመዝን እና ውሳኔ የማሳለፍ ሂደት ላይ አካባቢያዊ መሪዎችን የሚያሳትፍ መሪ የተሻለ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፥ ሞገስ ባላቸው መሪዎች ላይ ከመጠን በላይ ተስፋ ማድረግ እና ሀሳብን መጣል፣ ራሱን የቻለ አደጋ አለው። አንዳንድ ጊዜ፥ እንደዚህ ያሉ መሪዎች፣ ስልጣን የማጋራት ጥሪ በሚያደርጉላቸው መሪዎች ሊወሰዱ፣ ወይንም እስር ሊገጥማቸው ይችላል። እንደሁኔታው የሚለዋወጡ ወይም ወኪል የሚሆኑ እንቅስቃሴዎች የሚፈጠሩ ከሆነ ግን፥ መሪዎቹ አንድ ነገር ቢገጥማቸው  እንኳን እንቅስቃሴዎቹ ወደፊት ገፍተው፥ ተተኪ የሚሆኑ አዳዲስ መሪዎችን ሊያፈሩ ይችላሉ።

### 6. ሕዝባዊ ተቃውሞ አገሬ ላይ ውጤታማ ይሆናል ብዬ የማላስብ ከሆነስ?

ሕዝባዊ ተቃውሞ ሁልጊዜ አይሳካም። ነገር ግን፥ ልሂቃን እና ሌሎች አዋቂዎች ራሱ፥ ሕዝባዊ ተቃውሞ ወደለውጥ ጎዳና አያመራም ባሉበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር፥ በብዙ አገራት ተሳክቷል። የቺሊው ጄነራል

አገስት ፒኖቼ በዓለም ላይ በጣም አምባገነን ከሚባሉት ውስጥ የሚመደብ ነበር። ብዙዎችም ሕዝባዊ ተቃውሞ  እሱን ለመጣል ቁልፍ ይሆናል ብለው አልጠረጠሩም ነበር። ነገር ግን እንደዚያ ነበር የሆነው። እንዲሁም “የባልካናውያን አራጅ” (Butcher of the Balkans) በሚል ቅጽል ስም ይታወቅ የነበረው፣ የሰርቢያው አምባገነን መሪ ክሎቦዳን ሚሎሴቪክ፣ በሰላማዊ መንገድ ከስልጣን ይወርዳል ብለው ጥቂቶች ጠርጥረው ነበር። ቢሆንም ሚሎሴቪክ ወታደሩን እና ፖሊሶችን፣ እ.አ.አ በ2000 ዓ/ም፥ ከስልጣኑ እንዲለቅ ሰላማዊ ሰልፍ ያደርጉ የነበሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን እንዲጨቁኑ እና እንዲያፍኑ ቢያዝም፥ የደህንነት ኃይሎቹ የእሱን ትዕዛዝ ፈጽመው ክተት የወጣው የገዛ ሕዝባቸው ላይ የእሱን ትዕዛዝ ለመፈጸም እምቢ ብለው ነበር። ስለሆነም፥ ሚሎሲቪክ ከስልጣን ከመውረድ የተለየ አማራጭ አልነበረውም።

አሁንም እናንተ ባላችሁበት ነባራዊ ሁኔታ፥ ሕዝባዊ ተቃውሞ ውጤታማ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ እርግጠኛ መሆን ካልቻላችሁ፥ ሌሎች ሊፈጸሙ የሚችሉ አማራጭ መንገዶችን ከግምት መከተት ይቻላል። የፖለቲካ አሰራሩን ማስተካከልና ከውስጥ ማሻሻል፣ በምርጫዎች ላይ መሳተፍ፣ ለህግ ስርዓቱ አቤቱታ ማቅረብ፣ ከባላጋራ ቡድን ጋር ድርድር ወይም ስምምነት ማድረግ፣ ከዓለማቀፍ ድርጅቶች ድጋፍ ለማግኘት፥ አቤት ማለት፣ እንዲሁም የትጥቅ ትግል ማድረግ፥ በዓለም ላይ በተለያዩ ቦታዎች የተሞከሩ መንገዶች ናቸው። ሕዝባዊ ተቃውሞ ስለመሳካቱ እርግጠኛ መሆን ባይቻልም፥ ሌሎች አማራጭ መንገዶች ላይም እንዲሁ እርግጠኛ መሆን አይቻልም።

ለተቃዋሚ ቡድን ውሳኔው የሚሆኑት አማራጮች ከሚከተሉት መካከል ናቸው። የተሰባጠሩ የትግሉ ተከታዮችን የማፍራት ዕድል፣ የጨቋኙን የተአማኒነት ሁኔታ መለወጥ፣ ጭቆናን ማምለጥ ወይም ማለዘብ፣ ወይም ላለው ስርዓት ጥብቅና ለሚቆሙ ሰዎች የትግል የስራ ድርሻን ማከፋፈል ናቸው። በታሪክ ውስጥ እነዚህን አማራጮች ከግምት በማስገባት፣ በሕዝባዊ ተቃውሞ ለመሰማራት የመረጡ በርካታ የተቃዋሚ ቡድኖች አሉ። ነገር ግን አንዳንዴ በተጓዳኝ፥ እንደ ምርጫ፣ ህጋዊ ሂደት፣ ድርድሮች እና ስርዓቱን በማደስ በመሳሰሉ፥ ልማዳዊ በሆነው የፖለቲካ አሠራር ለውጥ ለማምጣት ተጠቅመዋል።

## 7. ባላጋራው የሃይል እርምጃ ቢጠቀምስ?

በሆነ ወቅት ባላጋራው ቡድን የሃል ጥቃትን ሊጠቀም እንደሚችል መጠበቅ ተገቢ ነው። በታሪክም ብናየው፥ ይኼ ለብዙ ጊዜ የሆነ ነገር ነው። ቢሆንም ግን ተቃዋሚው ፓርቲ ኃይልን ተጠቀመ ማለት፣ የሕዝባዊ ተጋድሎ እንቅስቃሴ ወድቋል ማለት አይደለም። የሕዝብ ትግል በተለያየ መንገድ ውጤታማነቱ ሊቀንስ የሚችል፣ እና ከሚፈለገው ውጤት የአጸፋው ምላሽ መልሶ ራሱን የሚጠቃ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ ይኖራል።

በመጀመሪያ፥ ጥቃት የተሞላበትን ጭቆና ለማስወገድ ወይም ድምጹን ለማዳፈን፥ የሕዝባዊ ትግል እንቅስቃሴዎች፣ በጥቃት እና በኃይል የተነሳ ለመዳፈን አስቸጋሪ የሆኑ ዘዴዎችን መጠቀም ሊጀምሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፥ ሰዎች የተወሰኑ፣ ዒላማ የተደረጉ ምርቶችን ላለመጠቀም ወይም ላለመግዛት አድማ ማድረግ፣ ለማፈን በጣም አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ማዕከላዊ ስላልሆኑ፣ እነማን ይሳተፉ እነማን አይሳተፉ መለየት እና ማረጋገጥ ለመንግስት ከባድ ይሆንበታል። የተቃውሞ ሰልፎች ወይም ሌላ ዓይነት

ሕዝባዊ ዘዴዎች የሚከለከሉ ከሆኑ፥ እንደ ግብርን እና የተለያዩ ክፍያዎችን ለመክፈል እምቢ ማለት፣ ወይም አጠቃላይ የሆነ ሕዝባዊ አመጽ ማድረግ ለእንቅስቃሴው የተሻለ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛ፥ የሕዝባዊ ትግል እንቅስቃሴዎች፣ የባላንጣቸው ጭቆና መልሶ ራሱን ጨቋኙን እንዲጎዳ የሚያደርጉ ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ። ጭቆናን ለዓለም ማጋለጥ፣ እንዲሁም ጭቆናን በፎቶዎች እና በትርክቶች ደግፎ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ፣ ዓለማቀፍ ተቀባይነትን እና የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በማሳጣት ረገድ ጨቋኙን ብዙ ዋጋ የሚያስከፍለው ነው የሚሆነው። በርግጥ ጭቆና በሙሉ መልሶ መልሶ ጨቋኙ ላይ አይከሸፍም። ነገር ግን አንድ የትግል እንቅስቃሴ ሲወሳሰብ፣ ሲዘገይ ወይም የጭቆናን የተወሰኑ መጥፎ የሆኑ ተግባራት የሚያጋልጥ ሲሆን፥ ውጤቱ ለጨቋኙ በጣም ከፍተኛ የሆነ የሕዝብንም የዓለም አቀፍንም ድጋፍ የሚያሳጣ ነው የሚሆነው።

ሶስተኛ፥ እ.አ.አ በ1986 ፊሊፒንስ ውስጥ፣ በ2000 ሰርቢያ እና በ2004 ዩክሬን ውስጥ እንደነበረው፥ የደህንነት ኃይሎቻቸው ከታጋዩ ሕዝብ ጋር በመወገን፣ የመንግስት ስርዓትን የመጨቆን አቅም የቀነሱ የሕዝባዊ ተቃውሞዎች አሉ። እነዚህ የደህንነት ኃይሎች ፍልሰት የተከናወነው፥ የመንግስት የደህንነት ኃይሎች ለስርዓቱ ያላቸውን ታማኝነት እንዲያሸሹ ታስቦ በተነደፉ፣ ሆነ ተብሎ፣ ረጅም ጊዜን በወሰደ የሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች ጥረት የተነሳ ነው።

## 8. ባላጋራን ማሳመን ቢያቅተኝ ወይም፥ አላምን ቢልስ?

ለማሸነፍ ዋነኛ ለጭቆናው ኃላፊነት መውሰድ የሚገባቸውን አካላት ማሳመን አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን የተወሰኑትን የጨቋኝን ደጋፊዎች ማሳመን አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

አስታውሱ! ሕዝባዊ ተቃውሞ ትልቅ አቅም የሚኖረው፥ ተግባራቶቻቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጭቆናውን የሚደግፍ የሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን እምነትና ባህርይ ስለሚቀይር ነው። የባላንጣው የኃይል ምንጭ ሲዳከም፣ አመነም አላመነም ብዙ ልዩነት አያመጣም። ባላጋራ በሚመጣው ነገር ሁሉ የመቆጣጠር አቅም እስከሚያጣበት ጊዜ ድረስ የባላጋራ አቅም ይቀንሳል። ስለዚህም፥ ለአዲስ ስርዓት እና ሽግግር ለመደራደር ይገደዳል።

ለምሳሌ፥ እ.አ.አ. በ1985 በደቡብ አፍሪካ የኤልሳቤጥ ወደብ፣ የፀረ አፓርታይድ ታጋዮች እንቅስቃሴ፥ በነጮች ይመሩ የነበሩ ንግዶች ላይ አድማ ማድረጋቸው፥ መንግስት አካሄዱን እንዲቀይር ጫና ለመፍጠር ጀምረው ነበር። ምናልባትም እነዚህ የንግድ መስኮች ከትግሉ ዓላማ ጋር ተስማምተው ላይሆን ይችላል። ነገር ግን የመንግስትን ጭቆና ከመደገፍ ይልቅ የታጋዮቹን ፍላጎት መቀበል የተሻለ ሆኖ አግኝተውታል።

## 9. ይኼ መንገድ ረዥም ጊዜን ይወስዳል። መታገስ ካልሆነልንስ?

ሕዝባዊ ተቃውሞ ተጽህኖ ለመፍጠር፥ አንዳንዴ ነው እንጂ ሁሌ ረጅም ጊዜ አይወስድም። ፊሊፒንስ ውስጥ አምባገነንነ የነበረውን ፈርዲናንድ ማርኮስን ከስልጣን በመጣል ረገድ፣ ከተቋቋመ አስር ዓመት ከነበረው የአንድነት የትግል እንቅስቃሴ (Solidarity Movement) አልተሳካለትም ነበር። ይልቅስ ከተቋቋመ ጥቂት ጊዜያት ብቻ አስቆጥሮ የነበረው የተቃዋሚ ትግል ነበር ያንን ማሳካት የቻለው። የአንድ

ሕዝባዊ ተቃውሞ ውጤታማነት የሚወሰነው፥ ብዙ ዓመት በማስቆጠሩ ሳይሆን፣ ትግሉ አንድነት ያለው እና ዘዴ የተሞላበት በመሆኑ ነው።

## 10. እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

የትግል እንቅስቃሴዎች ወይም ዘመቻዎች መጠነ ሰፊ የሆነ አንድነትን ማዳበር ከቻሉ፣ ዕቅዶችን በጥንቃቄ ከነደፋችሁ እና ኃይል አልባ ስርዓትን ለማዳበር ከቻለ፥ በጣም የላቀ የማሸነፍ ዕድል ይኖራል። አንድነት ወሳኝ ነገር ነው። ምክንያቱም የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች የብዙሃኑን ፈቃድ እና ድርጊት ያማከሉ ሲሆኑ ከፍተኛ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ በማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ፣ በፈቃደኝነት ላይ የሚመሰረት መሆኑን ማስታወስ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ መንስሄው ግልጽነት የጎደለው ወይም አጠራጣሪ ከሆነ እና እንቅስቃሴው አንድነት የጎደለው ከሆነ፥ ብዙዎች ራሳቸውን ከተሳትፎ ያገላሉ። በጥቅሉ፥ ስኬታማ የሆኑ የሕዝባዊ ተቃውሞዎች ወንዶችን እና ሴቶችን፣ ህጻናትን፥ ወጣቶችን እና አረጋውያንን፣ ከተለያዩ ብሔሮች እና ሀይማኖቶች የተውጣጡ፣ ተማሪዎች፥ ላብ አደሮች፥ ምሁራን እና ነጋዴዎችን እንዲሁም ሌሎች የማኅበረሰብ አባላትን በጋራ ያካትታሉ።

ዕቅድ አስፈላጊ ነገር ነው፤ ምክንያቱም የሕዝብ ተቃውሞ በዘመቻ፣ በእንቅስቃሴ፣ በሕዝብ ቡድን ወይም በቡድኑ ባላንጣዎች መካከል የሚደረግ ውድድር ነው። እንደዚህ ባለ ውድድር ውስጥ፥ ድርጅት ወይም ንድፈ ሀሳብ በአንድ ትግል የሚመራውን ኃይል ለማረቅ እና አቅጣጫ ለማስያዝ ይጠቅማሉ። በሕዝባዊ ተቃውሞዎች ውስጥ፥ መሪዎች ብዙ ንድፈ ሀሳቦችን እና ብልሃት የተሞላባቸውን ውሳኔዎች ያደርጋሉ። ለምሳሌ ያህል፥ ሀብታቸውን እንዴት ማካበት እና መጠቀም እንዳለባቸው፣ የባላጋራቸውን ድክመቶች እንዴት መለየት እና መጠቀም እንዳለባቸው፣ እንዲሁም የአጸፋ እርምጃዎችን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው ውሳኔ ያሳልፋሉ። ከስንት አንዴ ካልሆነ በቀር፥ መልካም ውሳኔዎች እንዲሁ በዘፈቀደ አይደረጉም። ጥሩ ዕቅድ ለመንደፍ፣ ሁለት ዓይነት የእውቀት አካሄድ ያስፈልጋል። በመጀመሪያ ንድፈ ሀሳቡን የሚያወጡት አካላት ስለሚገጥማቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ዝርዝር መረጃ እና እውቀት ያስፈልጋቸዋል። እንዲሁም ማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ቡድኖችን ፍላጎት እና ግብ ምን እንደሆነ መረዳት አለባቸው። ሁለተኛ፥ የትግል ንድፈ ሀሳብ አውጪዎች፣ ሕዝባዊ ተቃውሞ እንዴት እንደሚፈጸም ማወቅ አለባቸው። ይህንንም ከራሳቸው ልምድ፣ ከመጽሐፍት፣ ከፊልሞች፣ ከኢንተርኔት እና ከተለያዩ ምንጮች በሚያገኟቸው መረጃዎች፣ እንዲሁም በሕዝባዊ ተቃውሞ እና ፖለቲካዊ አደረጃጀት ዙሪያ ልምድ ካላቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሊቀስሙ ይችላሉ።

ኃይል አልባ የሆነ ግብረ ገብነት ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ባብዛኛው ሁከት ወይም ኃይል ጭቆናን ስለሚቀሰቅስ እና ስለሚያበረታታ፣ የተቃውሞውን ውጤታማነት ይቀንሳል። በተጨማሪም የተቃውሞ ትግል ኃይል ሲጠቀም፥ ብዙ ጊዜ የጥቃትን ስጋቶች መጋፈጥ የማይፈልጉ ማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ተሳትፎ ያጣል። በመስተመጨረሻም፥ አንድ የትግል እንቅስቃሴ፣ ፖሊስን ወይም ወታደርን በመቃወም የኃይል ጥቃትን ከተጠቀመ፥ ለስርዓቱ ታማኝ የሆኑትን የስርዓቱን ተሚጋቾች ለመከፋፈል አይቻልም። ጭራሽ በመንግስት ታማኝ ተከላካዮች ዘንድ፥ ለእንቅስቃሴው ሊኖር የሚችል ርህራሄ ይነጥፋል። ይህም የሕዝበ ተቃውሞው ሊያመጣ ይችል ከነበረው ዓላማ ተቃራኒ ነው። የእንቅስቃሴው ነጻ እና የተሻለ፣ ሁሉንም የሚጠቅም ማኅበረሰብ የመፍጠር ዓላማ፤ እንዲሁም የእንቅስቃሴው ተግባርም፥ ከሁሉም ዓይነት የተውጣጡ ድፍረት ያላቸውን ሰዎች ለትግል የመጥራት ተግባር፥ ስርዓቱ እንዲያበቃ ለሚፈልጉት ሰዎች እንደሆነው ሁሉ፣ ስርዓቱን የሚንከባከቡትን ሰዎች ልብም የሚያማልል ይሆናል።

## <u>ማራኪ ጥቅሶች</u>

“በእርግጥ በደቡብ አፍሪካ ለውጥ ያመጣው የብዙሀን በአንድ መደራጀት ነበር። ይሄ መንግስት መንግስት ላይ ጫና በማድረግ በስተመጨረሻ ለውጥ ለማስፈን እና መንግስት ምንም ዓይነት ምላሽ መስጠት ወደማይችልበት ሁኔታ አምርቷል።”

— ዶ/ር ጃኔት ፔሪ

“በትግል ውስጥ ዋነኛው ነገር ትኩረት ማግኘት ነው። ማንም ትኩረት ሊሰጥ በማይችልበት ጥግ ላይ መታገል፥ እንደባከነ እና ጥቅም እንደሌለው ጥረት የሚቆጠር ነው። እስከታገልኽ ድረስ፥ በቻልኸው መጠን ትኩረት መሳብ አለብህ።” — ምክሁሴሊ ጃክ

“ሃይል አልባ የሆኑ ትግሎች ጋር ከባዱ ነገር፥ በስነምግባር በደንብ የታነጸ እና ስልጠና፣ ንድፈ ሀሳብ እና እቅድ፣ ምልመላ እንዲሁም የትግል እንቅስቃሴን መሰረት አድርገው የሚከናወኑ ነገሮች አስፈላጊነት አይታያቸውም። ይሄም ብድግ ተብሎ ባንድ ጊዜ ሊከሰት አይችልም። በብልሀት መከናወን ነው ያለበት።” — ቆሞስ ጀምስ ላውሰን

“ለዚያ ነበር ጭቆናው መልሶ ከጥቅሙ ይልቅ ዶጂ የሆነው። ምክንያቱም፥ ልክ እንደ ሶስተኛው የኒውተን ህግ (the Third Newton Law) ለሁሉም ዓይነት ድርጊት እኩል ወይም ተቃራኒ የሆነ ግብረ-ድርጊት ወይንም ምላሽ አለው የሚል ነው። የጭቆናን መጠን እና ደረጃ ከፍ ሲሉ፥ ትግል እና ተቃውሞውም በዚያው ልክ ከፍ ይላል።” — ኢቫን ማሮቪክ